FCC Visit DTV.gov

# ወደ ዲጂታል ቲቪ መሸጋገር

## ስለ ዲቲቪ ምን ምን ማወቅ ያስፈልግዎታል




### ወደ ዲጂታል ቲቪ (ዲቲቪ) መሸጋገር ምንድን ነው?

ባሁኑ ወቅት፡ በአየር ላይ ያሉ ብዙ ጣቢያዎች ስርጭታቸውን የሚያስተላልፉት በአናሎግ እና በዲጅታል ቲቪ መልክ ነው። ከፌብሪዋሪ 17, 2009 በኋላ፡ ባለ ሙሉ ሃይል ቲቪ ጣቢያዎች ስራጭታቸውን የሚቀጥሉት በዲጅታል ብቻ ይሆናል። ወደ ዲቲቪ መሸጋገር በአየር ላይ በነፃ ቴሌቪዥን በሚያዩ ሰዎች ላይ (ጣራ ላይ የተሰቀለ ወይም "የጥንቸል ጆሮ" በሚመስል አንቴና የሚሠራ) ለውጥ ያስከትላል። እርስዎ በአየር ላይ የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች የሚያዩት በአናሎግ ቲቪ ከሆነ፡ ከፌብሪዋሪ 17, 2009 በፊት እርምጃ መውሰድ ይኖርብዎታል።

### የማሰራጫ ጣቢያዎች ወደ ዲጂታል የሚለውጡበት ምክንያት ምንድን ነው?

የአየር የግንኙነት መስመር ለፓሊስ፡ ለእሳት አደጋ፡ ለአስቸኳይ እና ፈጥኖ ደራሽ ግንኙነት ነፃ ለመልቀቅ የፌዴራል ሕግ ለውጡ እንዲደረግ ስላዘዘ፡ በተጨማሪም አሰራጪዎች የተሻለ ጥራት ያለው ምስል፡ ድምጽ እና የተለያዩ አማራጭ ፕሮግራሞች እንዲያስተላልፉ እና ሽቦ አልባ የሆኑ የንግድ አገልግሎቶች በስፋት ለደምበኞች እንዲያቀርቡ ለማድረግ ነው።

### ለመዘጋጀት ምንድን ማድረግ አለብኝ?

ሶስት አማራጮች አለዎ:

1. **የአናሎግ ቲቪዎን ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ጋር ያገናኙ።** ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥኖች በየሱቁ አሉ ዋጋቸውም አንድ ጊዜ የሚከፈል $40-$70 ነው። ለእነዚህ ሳጥኖች መግዣ ለመርዳት የዩ. ኤስ. መንግሥት ሁለት የ$40 ኩፓን ለአንድ ቤተሰብ በእርዳታ ያቀርባል። ስለኩፓኖቹ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.dtv2009.gov ይጎብኙ፡ ወይም ይደውሉ በ1-888-388-2009 (ድምጽ) ወይም 1-877-530-2634 (ቲቲዋይ) ይደውሉ። እንዲሁም፡ አሁን ባለዎት የስርጭት መቀበያ አንቴና የአናሎግ መስመሮችን 2-51 ስርጭትን በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ከሆነ፡ አዲስ አንቴና አያስፈልግዎትም። **ወይም**

2. **የዲጅታል ቴሌቪዥን ይግዙ (በውስጡ ዲጂታል ማዞሪያ ያለው ቲቪ)።** ዲጅታል የቴሌቪዝን ስርጭት ለማየት፡ ሃይ ዴፍኒሽን ቲቪ (ኤችዲቲቪ) አ<u>ስፈልግዎትም</u>። የሚያስፈለግዎት <u>ዲጅታል</u> ቲቪ ብቻ ነው (ወይም ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ጋር የተያያዘ አናሎግ ቲቪ)። እንዲሁም፡ አሁን ባለዎት የስርጭት መቀበያ አንቴና የአናሎግ መስመሮችን 2-51 ስርጭትን በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ከሆነ፡ አዲስ አንቴና አያስፈልግዎትም። **ወይም**

3. **በክፍያ የሚቀርብ የቲቪ አገልግሎት ያግኙ፡** የአካባቢ ስርጭቶችን እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ ካለ አቅራቢ በክፍያ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ከሆነ፡ ቴሌቪዥንዎ ለዲቲቪ ስርጭት ተዘጋጅቷል። የክብል ኩባንያዎች ማናቸውንም የስርጭት መስመራቸውን ወደ ዲጅታል የማሸጋገር ወይም የመቀየር ግዴታ <u>የለባቸውም</u>። ሆኖም እርስዎ አናሎግ ቲቪ ካለዎት በሚከፍሉት አገልግሎት ሰጭ በኩል የአካባቢ ስርጭቶችን <u>የማይቀበል</u> ከሆነ፡ በዚያ ቲቪ የዲጅታል የቴሌቪዝን ስርጭት ለማየት፡ ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ያስፈልግዎታል።

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት:**

1-888-CALL-FCC | DTV.gov | 1-888-TELL-FCC (TTY)